p″Ï ƒ K›″É ′ƒ ″ KÈ V ¡^ c=û `+
cT @ ›T @" ê ሰ ƒ
Kinijit for Unity and Democracy Party (Kinijit)
North America Office

በሰሜን አሜሪካ የቅንጅት ድጋፍ ኮሚቴ 2ኛ ጉባኤ የአቋም መግለጫ

በሰሜን አሜሪካ የቅንጅት ድጋፍ ኮሚቴ ተወካዮች ከሜይ 14 - 15፣ 2006 በዋሽንግተን ዲሲ፤ ሁለተኛ ጉባኤውን አካሂዶ፤ ቅንጅቱን ለማጠከር አስፈላጊ ናቸው ብሎ ያመነባቸውን የአደረጃጀት ለውጥ አድርጓል፤ ላዕላይ ምክር ቤቱንም በኦፊሴል ሰይሟል።

ከዚህም በተጨማሪ...

1ኛ - በወቅታዊ የኢትዮጵያ ጉዳዮች ላይ

2ኛ - በአገራችን የወያኔ/ኢህአዴግ አስተዳደር የሚያደርገውን ፀረ ህዝብ አፈና ግድያና ህገ-ወጥ እብሪት በመገምገም

3ኛ - የቅንጅትን የሰሜን አሜሪካ የድጋፍ እንቅስቃሴን አስመልክቶ የነበሩትን ጠንካራና ደካማ ጎኖች ገምግሞ፤ የሚከተለውን ባለ አስር ነጥብ መግለጫ አውጥቷል።

1 - የቅንጅት መሪዎች፣ አባላትና ደጋፊዎች፤ የኢትዮጵያ ነፃ ፕሬስ ጋዜጠኞች፣ የሲቪክ ማህበር አባላት ከሚገኙበት አስራት ያለአንዳች ቅድመ ሁኔታ እንዲፈቱ የሚደረገውን ጥረት አጠናክረን ለመቀጠል ቃል ገብተናል።

2 - ከምርጫው መጭበርበር ወዲህ፣ ተፋፍሞ የቆየውን የህዝባችንን ትግል፤ ከዳር ለማድረስ በየእለቱ ስቃይ ከሚደርስበት ህዝባችን ጎን እንሰለፋለን።

3 - በኢትዮጵያ ሰላማዊ የስልጣን ሽግግር ለማድረግ ከሚጥሩ ሃይሎች ጋር ሁሉ አብረን እንሰራለን።

4 - የውጪ ዲፕሎማሲው ስራ ይበልጥ በተቀላጠፈ መልክ እንዲከናወን፤ በያለንበት የአሜሪካ ክፍለ ግዛት አስፈላጊውን የሎቢ እንቅስቃሴ ለማጠናከር ወስነናል።

5 - በየአካባቢያችን ያለው ኢትዮጵያዊ በቅንጅት የአንድነትና የዲሞክራሲ ራእይ ዙሪያ ይበልጥ እንዲሰባሰብ ጥረታችን ይቀጥላል።

6 - የወያኔ/ኢህአዴግ አስተዳደር በውጭ የሚገኙ ኢትዮጵያዊያንን ትግል ለማኮላሸት የሚያደርገውን ሙከራ እናከሽፋለን።

7 - ቅንጅት የጀመረውን ከጥላቻ እና ከጎሰኝነት የፀዳ ፖለቲካ መሰረት በማድረግ፤ የወያኔ የዘር ፖለቲካ እንዲከስም ያላሰለሰ ሰላማዊ ትግላችንን እንቀጥላለን።

8- የቅንጅትን አቅም በሁሉም መስክ እናጠናክራለን።

9- ቅንጅት በአለም አቀፍ ደረጃ በሚያደርገው የሰላማዊ ትግል እንቅስቃሴ ውጤታማ እንዲሆን የኢትዮጵያዊነት ግዴታችንን እንወጣለን።

10 - ቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ ፓርቲ መሪዎቹ በእስር ላይ ይገኛሉ። ከነዚህ መሪዎች እውቅና ወይም ይሁንታ ውጪ የሚደረግ ማንኛውንም እንቅስቃሴ አጥብቀን እንቃወማለን።

"የሰሜን አሜሪካ ቅንጅት የድጋፍ ሰጪዎች ላዕላይ ምክር ቤት"
ዋሽንግተን ዲሲ፣ ሜይ 15፣ 2006።

766 Rock Creeck Church Road NW, Washington DC 20010
Tel. (202)541-9507, Fax: (202)541-1090, Email: kinijitUSA@kinijit.org